# አነግና  ተቃዋሚዎች በእውኑ ሕዝባችሁን ታውቃላችሁን?

ይነጋል በላቸው

ይሄን ሰሞን የነካኝን እንጃ ተጣላ ተጣላ ብሎኛል፡፡ ምን እሆናለሁ? መጣላቴ ግድ ከሆነ ልጣላ - ዕርቅ አለ አይደል? እንደለመድኩት ልክ ልኬን ሲያቀምሱኝ ብዕሬን እሰቅልና እገላገላለሁ፡፡ ከዚያ ዕርፍ! ባቄላ አለቀ ስንቅ ቀለለ ነው ተረቱ፡፡ ወደዛሬው መጣጥፌ ከመግባቴ በፊት በሰሞኗ ጽሑፌ አንዠታችሁ ‹ቅቤ የጠጣም› ያልጠጣም የተበሳጫችሁም ያልተበሳጫችሁም - በተለይ የምለውን ሁሉ እንደግል ጥቃት ያህል በመውሰድ ‹አንት ፋንድያ› እያለ ከምሩ እየተናደደ ውድ ስድቡንና ዘለፋውን የሚልክልኝና የሚያስቀኝ ወዳጄና በኢሜይል አድራሻየ ትችትና አድናቆታችሁን የላካችሁልኝ አንባቢያን ሁላችሁም ምሥጋናዬ ይድረሳችሁ፡፡ ጎበዝ - ለማንኛውም ግን ስድብ አይለጠፍምና ከስድብ ይልቅ ለቁም ነገር ቅድሚያውን እንስጥ - በበኩሌ እንደፈንጣጣ ስለወጣልኝ እስቅ እንደሆነ እንጂ በጭራሽ የሚሰማኝ ነገር የለም፡፡

ግራሃም ፒብልስ የተባለ በሀገረ እንግሊጣር የአንድ በጎ አድራጎት ድርጅት ዳይሬክተር ስለኢትዮጵያውያን መሪዎች ምሥጢራዊነት የጻፈውን የዜና ትንታኔ አሁን አንብቤ ጨረስኩ - ከኢትዮሚዲያ ድረ ገፅ፤ አንተ አብርሃ እጅህን ቁርጥማት አይንካው - ተባረክ(ውሸቴን እንዳይመስልህ!)፡፡ ዘሃበሻንም ያላነበብኩ እንዳይመስላችሁ፡፡ ይቺ ድረ ገፅ ግን እንዴት ነው እንዲህ እሳት እየሆነች የመጣችው ጃል? ሳላውቃት ኖሬ እንዴት ቀርቶብኝ ኖሯል! ትደግልን፤ ትመንደግልን፡፡ የየሰዓቱን ዜናና ሀተታ በወቅቱ እያቀረቡ ሕዝብን ያለ አንዳች አድልዖ ማገልገል እንደዚህ ያስወድሳልና ይህ ምግባር እምብዝም ባልተለመደባቸው የሚዲያ ማዕከላትም ተስፋፍቶና ተጠናክሮ እንዲቀጥል እየተመኘሁ ወደጀመርኩት ሃሳብ ልሂድ፡፡ ‹አንዳንድ ሥፍራዎች፣ ጥቂት ቦታዎች…› የሚለውን የሜትሮሎጂ ጥንቅር ለወጥ አድርጌ ‹ብዙዎች ሰዎች፤ አንዳንድ ዜጎች…› የምለው እንደነሱው በቂ መረጃ ከማጣት የተነሳ መሆኑን ዕወቁልኝ፡፡

ብዙዎች ኢትዮጵያውያን ስለሀገራቸው ሁኔታ ቅንጣትም አለማወቃቸው ብቻ ሳይሆን ለማወቅም ፍላጎት የማያሳዩበት አዝማሚያ እየተበራከተ ባለበት በዚህ ፈታኝ ዘመን ስለኢትዮጵያ የሚጨነቁና ጭንቀታቸውንም በሚዲያ የሚገልጡ እንደግራሃም ፒብልስ (ግራሃም ሀንኩክንም አንርሳ) ያሉ አንዳንድ አስተዋይ የዓለም ዜጎችን ማግኘት ያስደስታል፤ የእኛነታችንን ማንነትም እንድንጠይቅ ያደርጋል፡፡ ይህ ለየት ያለ አጋጣሚ የሚያሳየን ምንም እንኳን እኛ ኢትዮጵያን ብንተዋት ፈጣሪና ፍጡራኑ የማይተዋት መሆናቸውን ነው፡፡ ‹በትውልድ እንግሊዛዊ፣ በምርጫ ግን ኢትዮጵያዊ› ያሉትን የሪቻርድ ፓንክረስት ቤተሰብንም እናስታውስ፡፡ የዛሬውን አያድርገውና ኢትዮጵያን ከልባቸው የሚወዱና ቤት ንብረታቸውን ነቅለው ወደዚህች ቅድስት ሀገር(እንዳሁኑ ሳትረገም) የተሰደዱ የዓለም ዜጎች በርካታ ነበሩ፡፡ ዐረቦች በየጓሯቸው ነዳጅ እያወጡ እንዲህ በፔትሮ ዶላር ሳይናጥጡና የተቀረው ዓለም ላይ በጥጋብ እንትን እንበል ሳይሉ ኢትዮጵያ ነበረች መጠጊያቸው - ‹ሱቅ› ለማለት ‹ዐረብ ቤት› የምንለውን ስማዊ ጥምር-ቃል ልብ ይሏል፡፡ ያ ዘመን ይመለሳል!! መጽሐፋዊ ብሂሉም ‹ፊተኞች ኋለኞች፣ ኋለኞችም ፊተኞች ይሆናሉ› ይላልና ብዙም ተስፋ አንቁረጥ፡፡

ፒብልስ በጽሑፉ እንደጠቀሰው (እባካችሁን አንብቡት!!) ኢትዮጵያውያንና መሪዎቿ ሆዳቸው የማይገኝ እጅግ ምሥጢረኞች ናቸው፤ ሰውን የማያምኑና ለውጮች ብቻም ሳይሆን እርስ በርሳቸው ተጠራጣሪዎች ናቸው ይላል፡፡ ለነገሩ ያልዘሩት አይበቅልምና ከተጣራጣሪ ሕዝብ የሚወጣ መሪ ተጠራጣሪ ቢሆን አይፈረድበትም፡፡ ይህ ሰው ባወጣው ጽሑፍ የተጠቀሱ ጸሐፍት አሉ፡፡ የአንደኛውንና ስሙን ለማንበብ ሁልጊዜም የምቸገርበትን ፖላንዳዊ ጋዜጠኛና ደራሲ - ሪሳርድ ካፑሺንስኪ(የኔ ነገር - አወላግጄው ይሆን?) - የደረሰውን ‘The Emperor’ የተሰኘ አነስተኛ ጥራዝ ሳነብ የተሰማኝ ስሜት የቁጭትና የንዴት ነበር - ይህንንም ያላነበባችሁ አንብቡት  - አንብቡናም ትንሽ ተናደዱ፡፡ መቼ ነው ግን ሰው የሚወጣልን?  እኛ ኢትዮጵያውያን ያለን ባሕርይ ከሞላ ጎደል በመሪዎቻችን ላይ ግዘፍ እየነሳ ዞሮ ተመልሶ እኛኑ ያናፍለናል፤ ለማያባራ ሥቃይና መከራም ይዳርገናል፡፡ ስለዚህ ይህን ጠባያችንን - የግልጽነት ጉድለት፣ ለተሾመ ማሸርገድና ማጎብደድ፣ የበላይን በጭፍን መከተል፣ በግልጽ ውይይት ችግርን ያለመፍታት … ለማስወገድ ሱባኤ መግባት ሳያስፈልገን አይቀርም፡፡ ባህላዊ ሥነ ቃላችን ‹ሰማይ አይታረስ፣ ንጉሥ አይከሰስ› እና ‹ዐዋቂ ሲያወራ ልጅ ወደ ጓዳ› እያለ፣ ሃይማኖታችን ‹ለንጉሥህ ሰጥ ለጥ ብለህ ተገዛ› እና ‹የምንላችሁን ተቀበሉ እንጂ የምናደርገውን አትከተሉ› እያለ ከልጅነታችን

ጀምሮ ባሪያ አድርጎ ኮድኩዶ ስላሳደገን የምንጠላውን ነገር የመቃወም ድፍረታችንና በነጻ ሃሳብን የመለዋወጥ ባህላችን ድንክዬ እንደሆነ አለ፡፡

ከፒብልስ አቀራረብ እንደተረዳሁት ከአፄ ምንሊክ አሟሟትና የቀብር ምሥጢር በጉልኅ የጀመረው የመሪዎች ድመታዊ ገመናን የመሸፋፈን ምሥጢረኝነት አሁን ድረስ ልንፈታው ያልቻልነው የ21ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ዕንቆቅልሽ ሆኖብናል፡፡ ለዚህም ነው - እንደፒብልስም - በዛሬዋ ዕለት 55ኛ ቀኑን የደፈነው የጠቅላይ ምሥጢር መለስ ዜናዊ ወቅታዊ ሁኔታ አሁንም ሌላ ዕንቆቅልሽ ሆኖብን የሚገኘው፡፡ አፄ ምንሊክ ሞተው በምሥጢር ከተቀበሩ በኋላ - እውነት ይሁን ውሸት አላውቅም - ለሦስት ዓመታት በስማቸው ተገዝቷል ሲባል ሰምቻለሁ፡፡ አሁን መለስ እንደሚባለው በርግጥም ሞቶ ከሆነ በስሙ ለሁለት ወራት ያህል እንደተገዛን ይታወቃል፡፡ ሁኔታዎች በዚህ መልክ ከቀጠሉ አቶ መለስ ይፋዊ የቀብር ሥነ ሥርዓቱ ሳይፈጸም ምናልባትም ቀብሩ መፈጸሙም በባለጉዳዮቹ ግምት አግባብ ሳይሆን  እንደቀረ ብንገምት ከእንግዲህ ለስንት ዓመት እንደምንገዛ አላውቅም፡፡ በዚህ ዕንቆቅልሽ ዙሪያ እኔ በበኩሌ እየተማርኩ ያለሁት አዲስ ነገር ወያኔ/ኢሕአዴግ በርግጥም እባብና ምሥጥ መሆኑን ነው፡፡ በዚህ ዘመን እኮ ሰማይ ላይ ሆነህ አብርሃ በላይ ወይም ሄኖክ ዓለማየሁ - እኔስ ብሆን - የበላናት ቁርስ  ገና ወደደምነት ሳትለወጥ - ዱባም ትሁን ዕንቁላል - ዓይነቷን ከነ'nutritive value' የሚለይና ሪፖርት የሚያደርግ ቴክኖሎጂ አለ - ኢፓንጉኑ ይሆን? በሦርያ ዋና ከተማ ደማስቆስ አውራ ጎዳና ላይ በግል መኪናው ሲንሸራሸር የነበረውን የፍልስጥኤም ጦር ሁለተኛ መሪ በትራጀክተሪ ሚሳይል እንደገበረ ጉንዳን ከሚርመሰመሱ ሌሎች መኪኖች መሃል ተለይቶ የተመታውና ሕይወቱ ያለፈው በምን ጥበብ ነው? ታዲያ የታርጋ ቁጥርንና የመርፌን መጠን ከሺዎች ኪሎ ሜትሮች ርቀት የሚመነጥረው የ21ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የምዕራብና የምሥራቅ ቴክኖሎጂ በመሪያችን መሠወር እንዲህ ከፋኛ ስንጨነቅ ምን ዋጠው ይባላል? በወያኔስ እንዴት ሊረታ ቻለ? ይሄ ምሥጢር አያስደንቅም ትላላችሁ? ግን ‹ዐውቆ የተደበቀ ቢጠሩት አይሰማም›ንና ‹ወርቅ የተጫነች አህያ የማትደረምሰው ምሽግ የላትም› የሚሉትን ብሂሎች አሰላስሏቸውና ምሥጢሩን በነዚህ አባባሎች ውስጥ ተሰንቅሮ ታገኙታላችሁ፡፡ አልኩ ለማለት እንጂ አሁን ይህን ማን ያጣዋል? አይ የኛ ገንዘብ! አስከሬን መደበቂያም ይሁን?

እነሱ ሳያስቡትና ተተኪ ሳያዘጋጁ ፈጣሪ ደረሰና ጉድ አፈላባቸው - እነሱ የምለውን ከሀገር ውስጥ የወያኔ ምንደኞች  አውጡልኝ - እነሱ ‹ሲጠሯቸው አቤት፤ ሲልኳቸው ወዴት› የሚሉ  የነእንቶኔ ጉዳይ አስፈጻሚዎች እንጂ የራሳቸው ኅልውና የሌላቸው በድኖች ናቸው፡፡ እናም በድንገቴው ተደምመው በፈጣሪ ሥራም ተገርመው በአፍ ትምተማ አንዳቸው ከአንዳቸው በመግባባት ዝምታን መረጡ፤ አለበለዚያስ እውነቱን ያውቁታል፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትሩ የዓመት ፈቃድ ላይም ሆነ ከህመም የማገገሚያ ፈቃድ ላይም ሆነ ወደአካፑልኮ ቤይ ለክረምት ሽርሽርም ይሂድ ሃቁን ያውቁታል፡፡ ያስቸገራቸው አንዱን መርጠው ጠቅላይ ተላላኪው አቶ መለስ ለሚጨነቅለት ሕዝብ ማሳወቅን ነው - እናንተዬ የትልቅ ሰው መርዶ እኮ ይከብዳል - ትልቅ ሰው ‘ in a sense’ ሰውዬው ባለው ፖለቲካዊ ተፅዕኖ ማለቴ ነው - አማርዝኛው እኔስ እያማረኝ  ለምን ይቅርብኝ? የሰውየውን የትነት  ማወቅ ደግሞ መብታችን ነበር፤ ነውም እንጂ፡፡ እንኳን የሀገሬን መሪ የዕድሬንም መሪ ሁኔታ የማወቅ መብት አለኝ፡፡ ግን ‹ሚስትህ ወንድ ወለደች ወይ› ቢለው ‹ማንን ወንድ ብላ› እንዳለው ቢጤ ሆኖብን ነገሩ የተወሳሰበ ሁኔታ ላይ የሚገኝበት ሁኔታ ላይ ነው ያለው - በወያኔ ቋንቋ፡፡

የፈጣሪን ሥራ ግን ዝም ብላችሁ ተመልከቱ፡፡ ከንቱ ሰው ብዙ ያስባል፡፡ ሊገድልህ ብዙ ያደባል፡፡ ሊያጠፋህ ብዙ ይማስናል፡፡ መሞትህ የማይቀረውን ሞት ቀደም ብሎ ሊሰጥህ ያለ የሌለ ሀብትና ንብረቱን ያባክናል፡፡ ለውድቀትህ መቶ ዓመትም ቢሆን ቆይቶ የሚፈነዳ ቦምብ ይቀብርብሃል፡፡ በመካከልህ ፈርጀ ብዙ ፈንጂዎችን አጥምዶ በራስህ ጊዜ ካምሱሮቹን እየነካካህ እንድትተላለቅ ያሤርብሃል፡፡ በዚያም ሥራው እየተደሰተ በሣቅና በሁካታው ያደነቁርሃል፡፡ ያ መሠሪ ጠላት የማያውቀው ግን የፈጣሪን ፈራጅነት ነው፡፡ አሁን እግዚአብሔር በኢትዮጲያ ጉዳይ በግልጽ እየፈረደ አይደለም ብሎ የሚከራከር ሞኝ አለ? ይኖር ይሆናል - ግን መኖር አልነበረበትም፡፡ በገሃድ እያየነው? ችግሩ ‹ዐይን አላቸው ግን አያዩም፤ አፍንጫ አላቸው ግን አያሸቱበትም፤ እግር አላቸው ግን አይሄዱበትም...› ተብሎ ለአሪታውያን የጣዖት ቅርፆች እንደተነገረው እኛም ሁሉም የስሜት ሕዋሳት እያሉን የማስተዋል ጥበብን ስለተነጠቅን ነው - ከሞላ ጎደል ሁላችን፡፡ እንዲያ ባይሆን - እንዲያው ለምሳሌ - የነገ ሚች የዛሬን ኅያውና የነገን ሚች ለምን ይገድላል?

እኔ ቀደም ካለ ጊዜ ጀምሮ የተረዳሁት አንድ ነገር አለ፡፡ ኢትዮጵያን ለአጎዛነት እንደሚዘጋጅ ቆዳ ወጥረው የያዙ ሦስት ሰዎች ነበሩ - አሉም፡፡ ከነዚህ ሦስት ሰዎች ሁለቱ በእግዜር እጅ መያዛቸውን እየሰማሁ ነው(እንዲያውም ይህን ደብዳቤ ልልክ ስል አንዱ

ወዳጇ ማረፋቸውን ሰማሁ ብሎ መይሎልኛልና እውነት ከሆነ ዘመቻ ሃራ ኢትዮጵያ ተፋፍሞ ቀጥሏል ማለት ነው፤ ቤተ ክርስቲያንም ተዋርዳብን ነበርና እሷም ሕጽበት ያሻታል)፡፡ ጊዜ ገቢር ለእግዚአብሔር - ሃሌ ሉያ፡፡ ይህ አጋጣሚ ሰው ሠራሽ ነው ወይንስ ከፈጣሪ? ምን ዓይነት ታሪካዊ ኹነት አገጣጠማቸው? እሺ - አንደኛውስ ዕድሜው በመጫኛ ሥፍርም ስለማይደረስበት በዕድሜው ነው እንበል፡፡ ሌላውና ለተጣለብን የቤት ሥራ ዋነኛው አካል ግን ገና 57 ዓመቱ ነው - ወጣት ሽማግሌ፡፡ ብዙ መሥራት የሚችልበት አፍላ ዕደሜ ላይ ነው የነበረ፡፡ ሞተ አልሞተ ለጊዜው በምሥጢር እንደተያዘ እንተወው - ምርጫም ስለሌለን፡፡ በሽርሽርና በህመም ፈቃድ እንደዚህ ደብዛው ይጠፋል ብሎ ማመን ግን በትንሹ ቡልሃነት ነው - የሞኝነቶች የመጨረሻ ደረጃ፡፡ የዛሬ ሁለት ወር ገደማ ሽርተቴ  እንደያዛት ፍየል ሰውነቱ አልቆና ዐይኑ ብቻ ፈጥጦ በቁም የሚንቀሳቀስ ሬሣ መስሎ የነበረ መለስ ዜናዊ እያገገመ ነው ሲባል ��እውነታው በፈረንጅኛው አገላለጽ�� ‘is even too faint to give it  the benefit of the doubt’. እናም ይቺ የበረከት ስምዖን ጨዋታ ምናልባት ለሁለተኛ የልቦለድ መጽሐፉ መደጎሚያ እንድትሆነው ካላስቀመጣት በስተቀር  ቅሽም ያለች ቀሺም አመክንዮና እጅግ የመሸባት ቧልታይና ድንቃይ የልጆች ተውኔት ናት፡፡

ይሁን ግዴለም - ለነበረከት መለስ ጤናማ ይሁንላቸው፡፡ ‹ሞኝ እንዴት ያሸንፋል› ቢሉ ‹እምቢኝ ብሎ› ይባላልና፡፡ ሊመከሩበት የሚገባቸው ጉዳይ ግን ይህን ከላይ የመጣንና ቀጣይነቱም አስተማማኝ የሚመስል የእግዜር ዱላ ማንም አይችለውምና ቢቻላቸው አንዳች መፍትሔ ይፈልጉ፡፡ መደናበሩና ለተጨማሪ ጥፋት ደፋ ቀና ማለቱ በፍጹም አያዋጣም፡፡ እባብ ጭንቅላቱ ከተመታ በኋላ በቀቢፀተስፋ የሚያደርገው ሁሉ ሞቱን ያፋጥን እንደሆነ እንጂ የሚጠቅመው ነገር የለም፡፡ ነገር ግን ሌላው ሕዝብና ተቃዋሚ መረዳት ያለበት ቁም ነገር የተመታ እባብ ዝም አይልም፡፡ የነጋበት ጅብም ዝም ብሎ አይሄድም፡፡ የቆሰለ ነብርም ቁስሉን አዝሎ አይቀመጥም፤ ከፍተኛ ጥፋት  ያደርሳል፡፡ እየሞተ ያለን ያረጀ ሥርዓት እጅን በተገቢው ጓንት ሸፍኖ አፍንጫንም ጠቅጥቆ በጥንቃቄ መገነዝ ይገባል፡፡ ሃይማኖቱንም፣ ፖለቲካውንም፣ ንግዱንና ኢኮኖሚውንም ለመቆጣጠርና ወደተፈለው ወያኔያዊ የጉዞ አቅጣጫ ለማቀጣጨት የዛሬ 21 ዓመታት ገደማ የተጀመረው ዘርፈ ብዙ ብሔራዊና ዓለም አቀፋዊ ዘመቻ እየተጠቃለለ ነው (ብለን ማመን እንችላለን)፡፡ ይሄኔ አታጋፍጠኝ፣ አታጋትረኝ ነው ማለት፡፡ ከኑግ የተገኘሽ ሰሊጥ አብረሽ ተወቀጭ ነውና ለዚህ በቁሙ በስብሶ ለሞተ ሥርዓት የሚወረወር አንዳች ነገር እንዳይጠልፈን መጠንቀቅ ይገባል፤ እንጂ ሥርዓቱማ ፀጉራም ውሻ አለ ሲሉት ይሞታል ዓይነት ከሆነ ቆየት አለ - ጣር ስንት ቀን ይፈጃል ግን? አይ ጋሽ ፀጋዬ ምነው አሁን በኖረና በዚህችም ላይ በተቀኘባት! ሳልረሳው - ደርግ እኮ በቅጡ መሞት የጀመረው ግንቦት 8 ቀን 2001ዓ.ም ከተሞከረው መፈንቅለ መንግሥቱ ዕለት ጀምሮ ነው፡፡ እናም የወያኔው ሥርዓት ግብኣተ መሬቱ ሊፈጸም በጣም ተቃርቧል፡፡ እንዲህ የምለው እውነቴን ነው አንዳች ነገር በል በል እያለኝ እንጂ - የታሪክን አካሄድ በመረዳቴ እንጂ -  የጸሎትንና የልቅሶን የዞረ ድምር ውጤት  በመገንዘቤ እንጂ - ያለቀሰ መሳቁ ያስለቀሰም ማልቀሱ ነባራዊ እውነት መሆኑን በማሰብ እንጂ - አንዲት ጠመንጃም ይሁን አንካሴ  ይዞ ወደአዲስ አበባ - ወደፊንፊኔ - ፊንፊኔ? – (እመጣበታለሁ) - የሚገሰግስ የነጻነት አርበኛ እንዳለ ከመረዳት ወይም ከመገመት አኳያ አይደለም፡፡ የነጻነት አርበኛ ምን አስፈለገ? የፈጣሪ ጦር ከሰማይ የኢትዮጵያን ጠላት አናት አናቱን እያነጎደ ሲጥለው እያየን ምን ጦር ያስፈልጋል? ራሴኑ ልቃረን - ጦርማ ያስፈልጋል፡፡ ጠንካራ ጦር - ከሁሉም ወገን በብቃትና ችሎታ መሥፈርት የተውጣጣና በአንደነት መንፈስ የተዋቀረ ጦር - የሠለጠነ ጦር - ከዘረኝነት አሮንቃ የወጣ ጦር - በአንዲት ሀገር ጥላ ሥር የሚሰለፍ ጦር - በጎጣዊና ክልላዊ- በነገድና በቋንቋ ስሜት ያልታወረ ዘመናዊ ጦር ያስፈልጋል፡፡ በጎጠኛ ስሜት ተነሳስቶ አንዱን ለአንዱ ለማስገበር ሳይሆን በብሔራዊ ኢትዮጵያዊ ፍቅር የነደደ ሁነኛ ጦርማ ያስፈልገናል፡፡ ያማረ ንግግርና ውብ ተጠየቃዊ አካሄድ በገለልተኛ ጦር ካልታገዘ ጉልበተኞች እየተፈራረቁ ሲፈነጩብን ይኖራሉ እንጂ ወደምናልመው የጋራ ራዕይ ባፋጣኝ መድረስ አይቻለንም፡፡ ስለዚህ በዚህም ረገድ ይታሰብበት፡፡

ሃይ ተቃዋሚዎች! እንዴት ናችሁ? ስንተ ናችሁ ማለቴ አሁን ምን እየሠራችሁ ነው? አሁንም ሕዝቡ እናንተን አንጋጦ ይጠብቅ ወይንስ ሌላ ሙሤ እንዲልክለት ፈጣሪውን ይጠይቅ?   የት ናችሁ? አሮጌውን ወይን በአዲስ አቅማዳ ለመገልበጥ እየተዘጋጃችሁ ነው ወይንስ ማርሽ ልትለውጡ አስባችኋል? ሞቱ የሚደበቅ፣ ቀብሩ እማይታወቅ፣ በብሔራዊ ሀዘን ባንዲራ ዝቅ ብሎ የማይውለበለብለት፣ ብሔራዊ ሀዘን የማይታወጅለት፣ በስደት የሚማቅቅ፣ በዘረፋና በግድያ ወንጀል ስሙ የሚቦጨቅ፤ ከቤተ መንግሥት በወጣ በገባ ቁጥር በቅልብ ጦር ሕዝቡን ወደግድግዳ እያዞረ የሚያንቀጠቅጥ ተረኛ ንጉሠ ነገሥት ለመሾም ተዘጋጃችሁ ወይንስ እንደነ ዴቪድ ካሜሮን

በሕዝብ ትራንስፖርት እየሄደ ህመማቸውን የሚታመምና ደስታቸውን የሚካፈል መሪ እያሰናዳችሁ ነው? እንደስብሰቴው ዘመን በሥልጣንና በጥቅም፣ በቋንቋና በዘር፣ በአብሮ አደግና ባምቻ ጋብቻ እየተቀላለፋችሁ ወደሥልጣን ለመምጣት አቅዳችኋል ወይንስ በብቃትና በዕውቀት፣ በአመራር ጥበብና ዕድሜና ልምድ በሚሰጡት ብስለት ራሳችሁን አርቃችሁ(‹ር› ትጥበቅ) ሕዝባችሁን በቀናነት ለማገልገል ባጭር ታጥቃችሁ ወር ተራችሁን እየተጠባበቃችሁ ናችሁ? የምጠይቃችሁ አንድ ቁጫጭ ዜጋችሁ ነኝ፤ የምወክለው ግን በሚሊዮን የሚቆጠሩ ድምጽ አልባ  ምንዱባን ወገኖችን ነውና በተለመደው ኢትዮጵያዊ ድንቅ ባህላችን ‹እሱ ደግሞ ማን ነው? በሚለው የተዓቢዮ ንግግር ተሸንፋችሁ ጆሮ ዳባ እንደማትሉኝ በመተማመን ነው፡፡ አንዱ ባንዱ እየሳቀ የሚገባው የጀምበር ብዛት የሚያናድደን ወገኖች ብዙ ነንና አስቡልን፡፡

ትናንት ማታ አንድ መጠጥ ቤት ነበርኩ፡፡ ብዙ ሰው ያውካካል፡፡ መጠጥ ቤት ውስጥ የማይተዋወቀውም፣ የሚተዋወቀውም፣ ጆሮውም፣ የተቃዋሚ ደጋፊውም ስለሚኖር በራስ ተማምኖ ስለ ፖለቲካ የሚያወራ የለም፡፡ እጅግ ሲበዛ ፈሪ ሆነናል፡፡ ገና ብርጭቆ እንደያዝኩ ምን እንደነካኝም ሳላውቅ አንዱን ኦሮምኛ ተናጋሪ ድንገት አፌ እንዳመጣልኝ ‹ይሄውልህ ወንድሜ፣ አንተ አሁን ኦሮሚያ የሚባል ሀገር ከኢትዮጵያ ተገንጥሎ ብቻውን ነጻ ሀገር ቢሆን ትደግፋለህ?› ብዬ ጠየቅሁት፡፡ መልሱም የሚገርም ነበር፡‹ ‹ምን ማለትህ ነው? የቱ ነው ከየት የሚገነጠልና የራሱን ግዛት የሚያቆም? ማን ከማን ተለይቶ?› ነበር ያለኝ፡፡ የሌሎችን  ትኩረት መሳቤን ስረዳ መፈራራት እንደሌለብን፣ የሀገራችን ጉዳይ የኛም መሆኑን፣ ጨዋታችን ሁሉ በስም አይጠሬ የምንትሴ የምንትሴ ብቻ ሳይሆን ቁም ነገር አዘልም መሆን እንደሚገባው ለነገር አሳባቂዎችም በማይጎረብጥ መንገድ አስረዳሁና የሆነ እፎይታ አግኝቼ ጉብቴንም ቢያንስ የአንድ ቀን ዕድሜዋን አሳጥሬ ወደቤቴን ገባሁ፡፡ እንዴ፣ በምን እንደበቅና ይህን አስጨናቂ ዘመን ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን እንርሳ? ችግሩ የ0.85 ሣንቲሙ ነጠላ ድራፍት አሁን ብር አምስት መሆኑ፡፡ የዋጋ ነገር አይነሳ! ብዙዎቻችን የቅቤ ቅሎቻችንንና የሥጋ ቢላዎቻችንን አጣጥፈን ሰቅለናል - ደገኛ ዘመን እስኪመጣና የሚመጣም ከሆነ፡፡ ቆሎ ያረረበትንማ ቤቱ ይቁጠረው፡፡ ይህን ኑሮ ብለን እየኖርን ነው እንግዲህ፡፡

ሄሎ ኦነግ! የት ነው ያለኸው? ዕድሜህ ስንት ነው? ሎራን ካቢላ በአሥራ አንድ ወራት ጊዜ ውስጥ ኪንሻሳን ሲቆጣጠር አንተ በዚህ ረጂም ዕድሜ ከራስህ ጋር ከመፋለምና ራስህን በአንጃዎች ከመከፋፈል ባለፈ ለኛ ምን ሠራህ? ኧረ ለመሆኑ እኛን ታውቀናለህ? አትኩራ - አናግረኝ፤ ሁላችንም በመጨረሻው ባዶ ሆነናልና የሚኮራም የሚያስኮራም ነገር የለም፡፡ ግዴላችሁም ዛሬ ነገር ነገር ብሎኛል የደግ ያድርግልህ በሉኝ፡፡ እኮ አሁን የት ነህ - አባባ ኦነግ?

እናሳ፣ ኦነግም ሆንክ ሌላው ተቃዋሚ ሁላ ቀድመህ ለምን የሕዝብህን ፍላጎትና ስሜት አትረዳም? እግሩን የሚያሳክከውን ሰው ራሱን ቢያኩት ምን ይጠቅመዋል? አሁን የሕዝቡ ችግር ምንድነው? መገንጠል ነው? ራስን በራስ ያለመግዛት ችግር ነው? የሕዝበ ውሳኔ ጣጣ ነው? ቀድሞ የመቀመጫን አለች አሉ ጅንጅሮ፡፡ ይህን መሰሉ ነገር እኮ ለሰለጠነው የዓለም ማኅበረሰብ እንጂ የእግረኛ መቋረጫ ዜብራ መንገድ ላይ ተገናኝቶ ጉንጮቹን አገለባብጦ እየተሳሳመ የቤተሰብ ናፍቆቱን በሚወጣና ምሳውን ቀምሶ ለራቱ የሚጨነቅ የማኅበረሰብ አባል በሞላበት ኋላ ቀር ሀገር ውስጥ አይደለም፡፡ እዬዬም እኮ ሲደላ ነው፡፡ እናንተ ያያችሁት አውሮፓን ነው፤ እናንተ ያነበባችሁት የአሜሪካንንና የመሰል ሀገሮችን ታሪክ ነው፡፡ እኛን ሕዝባችሁን - ሕዝባችሁን ማለትም ከቻልኩ ነው - በጭራሽ አታውቁንም፡፡ እንደባበቅ አታውቁንም ነው የምላችሁ፡፡ ለምሳሌ እንደኔ በዕድርና በሰንበቴ፣ በጽዋ ማኅበርና በዕቁብ ከተለያዩ ዘውጎች አባላት ጋር ተገናኛላችሁ? እየበጠበጠን ያለው ትንሽ ዕውቀት ነው፡፡ ትንሽ ዕውቀት አደገኛ ነው መባሉ ለዚህ ነው - እኔ በትንሽ ዕውቀቴ ቢያንስ ሕዝቡን እንወቀው እያልኳችሁ ነው፡፡ እናንተስ? ሕዝቡ ዳቦና መሠረታዊ ዴሞክራሲያዊ መብቱን እንጂ እናንተ ከሌሎች ሀገራት ኮርጃችሁ ሸቅብ አጡዛችሁ የለቀቃችሁትን እንደደሮ ብልት ሀገርን የሚበጣጥስ የታሪካዊ ጠላቶች አጀንዳ የሚፈልግ ይመስላችኋል? መቼ ነው የሕዝቡን ፍላጎት ከቁብ መቁጠር የምትጀምሩት? መቼ ነው ላለፈ ክረምት ቤት መሥራታችሁን የምታቆሙት? መቼ ነው የነጎበናና ምንሊክ፣ የነአባመላና ባልቻ አፅም በሰላም እንዲተኛ ፈቃደኞች የምትሆኑት? ከአቡኑ በላይ ካቶሊክ መሆን የሚቃጣችሁ ጥቂት የማትባሉ የኦነግ አመራር አባላት ደግሞ ነፍጠኞች ከምትሏቸው የመሀል ሀገር ሰዎች የተካለሳችሁ ናችሁ፡፡ የ‹ክልስ› ደም ደግሞ ሞቃት ነው - በረት ይበጠብጣል፡፡ መለስና ኢሳይያስ ኢትዮጵያን ያመሱት የጥቁር ክልሶች ስለሆኑ ሳይሆን ይቀራል? በአንጻራዊ አነጋገር ከአንድ የትውልድ መስመር በሕጋዊ ጋብቻ የተገኘና በጥሩ ሥነ ምግባር ያደገ ዜጋ በአብዛኛው መልካም ዜጋ የመሆን ዕድሉ የሰፋ ነው (ተብሎ ቢታመን በተወሰነ ደረጃ እውነትነት ያለው ይመስላል)፡፡ ይሄ እየበጠበጠን ያለ የ1940 እና 1950ዎቹ ትውልድ ከባህሉም

ከሃይማኖቱም ከቤተሰቡም የተጣላ ፈረንጅ አይሉት ሀበሻ በመሀል ቤት በማንነት ኪሣራ የተዘፈቀ አጉል ትውልድ ነው - መቆሚያ መቀመጫ እያሳጣን ያለው፡፡ ያ የጠፋ ትውልድ ነው እያመሰን የሚገኘ፡፡ ደግነቱ እያረጀና በበሽታም በእርግማንም እያለቀ ነው፡፡...

ብዙ ኦሮምኛ ተናጋሪ ጓደኞች አሉኝ፡፡ እኔ ራሴም ኦሮሞ ነኝ፡፡ ለዝርዝሩ ጊዜ የለኝም፡፡ ከልጆቼ አንዱ 25 በመቶው ኦሮሞ ነው - ቢያንስ በዚህች የሳሳች የምትመስል እኔነት አልደራደርም - ኦሮሞ ነኝ፤ የደም ልጇ መከፋት የኔም ነው፤ የደም ልጇ መጎሳቆል የኔም ነው...፡፡ ኦሮሞ ያልሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ራሱ 80 በመቶው ኦሮሞ ነው፡፡ ምንጭ መጥቀሻ ጊዜ የለኝም፡፡ ታዲያ ማንን ነው ከማን እንገንጥል ብለን ከእውነት ጋር እንደ ዶን ኪኾቴ ምናባዊ የጨለማ ጦርነት የምንገጥመው? ሕዝቤ ተራበ፤ ተጠማ፤ ተበደለ፤ ተጨቆነ ፤ ፍትህን ተጠማ ... ብሎ ዘር ቀለም ሃይማኖት ነገድ ሳይለዩ ጫካ መውጣትና መታገል ያባት ነው፡፡ ነገር ግን ለመቶዎች ዓመታት የተጋባን፣ የተዋለደን፣ የተዛመደን፣ የተጋመደንና ልዩነቶቹን አቻችሎ በመተሳሰብና በመፈቃቀድ እየኖረ ያለን ሕዝብ ግለሰባዊና ቡድናዊ የልዩነት ቀዳዳዎችን በላይዳና በመንሽ በማዝራትና ልዩነትን ለማጥበብ ከመሞከር ይልቅ ይበልጥ እያንቦረቀቁ በማራገብ ከታሪክ ጋር ፍልሚያ መግጠም በእጅጉ ያሳዝናል፣ ይዋል ይደር እንጂ ለተጠያቂነትም ይዳጋል፡፡ በቅርቡ የተናገርኩትን የተውሶ አባባል እዚህም ላይ ልድገመው፡- ስህተት በስህተት አይቃናም፡፡ ታሪካዊ ጥፋቶች ከየትኛውም ወገን ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን ጥፋት ባጋጠመ ቁጥር እንደሕጻናት የቃቃ ጨዋታ ሀገርን በሚያህል ትልቅ ጉዳይ ‹ጨዋታው ፈረሰ ፤ ዳቦው ተገመሰ› እየተባለ መበታተንን በራሳችን ላይ ልንጋብዝ  አይገባም፤ ኃጢያትና ወንጀልም ነው፡፡ በዚያ ላይ በጦርነት ያልተገነባን ሀገር ፈልጉና አግኙ፡፡ ኦሮሞም በጦርነት ነው መላዋን ኢትዮጵያ ያዳረሰው፡፡ ምን አዲስ ነገር አለ? ጣሊያን እንኳን ጋሪባልዲ በሚባል ሰው አይደለም እንዴ ከ37 ይሁን ከ38 ቁርጥራጭ ጣሊያኖች የተሠራችው? ሞኝ እንደያዘው ፈሊጥ ከመቶ ምናምን ዓመታት በኋላ ምንሊክ፣ ምኒልክ መባሉ ምን ማለት ነው? የኢትዮጵያ ታሪክ ከሌሎች ሀገራት ታሪክ የተለዬ ነውን? ሳይረፍድ ወደዬጎሊናችን እንመለስ፡፡ አለበለዚያ እኔም ደብረ ታቦርን እገነጥልና እያንዳንድሽ ዋጋሽን ታገኛታለሽ! ስኮላርሺፕ አንሰጥ፣ ዕርዳታና ብድር አንፈቅድ፣ በቃ ... የደብረ ታቦርና አካባቢዋ ፌዴራል ዴሞክራቲክ ሪፑብሊክ፡፡ የኦነግ ምኞትና ሕልምም ከዚህ አይሻልም፡፡ ይህን እውነት ሕዝቡም ያውቃል፤ መናገሪያ ዕድልና መድረክ አጣ እንጂ፡፡

ሕዝቡ - ኦሮሞም በሉት ትግሬ አማራም በሉት ጉራጌ ስለግንጠላ ሲነሳ ይስቃል፤ በፖለቲከኞች ጅልነትና መሠሪነትም ይገረማል፡፡ በተለይ በተለይ ኦሮሞ የተሠራጨበትን የመሬት የቆዳ ስፋት ስንመለከት ኦሮሞን እንገንጥል ማለት ህልም እንጂ እውን አይመስልም፡፡ የቱን ከየትኛው? አንድ ወዳጇ ሰሞኑን በመየለልኝ ጽሑፍ ውስጥ የዲማ ነገዎን አንጀት ቆራጭ የጀርመን ሀገር ንግግር ስመለከት ተናደድኩ፤ በእግዜሩ ፍርድ መዘግየትም ተበሳጨሁ - ለኛ ረጂም ለርሱ ግን ተገቢ በሆነው ሰዓቱ መምጣቱ ላይቀር፡፡ ኦነግ ፊንፊኔን ያኔ እንዳለው ‹ሲቆጣጠር› (አሁን ምናልባት ቢቆጣጠር) ኦሮሞ ያልሆኑት ዜጎች ከከተማዋ እንዲወጡ ኮሪዶር ይዘጋጅና ውልቅ ይላሉ ነበር ያለው፡፡ ከፎከረ ቀርቶ ከወረወረ ለሚያድን የኢትዮጵያ አምላክ ምሥጋና ይድረሰው፡፡ የፀሐዬ ዮሐንስ ዘፈን ብልጭ አለብኝ አሁን፡፡ ግጥሙ ጠፋኝ - ግን ፈጣሪ ጠላቶቿን አንድ ባንድ በእግሯ ሥር ያውላል ዓይነት ነው ጭብጡ፡፡ እናሳ? አንድ ሰው ካላበደ በስተቀር የአንድ ከተማን ሕዝብ አሰለፎ ከኖረበትና እትብቱ ከተቀበረበት ሥፍራ ያስወጣል? ሰው መቼ ነው ሰው እሚሆን ጎበዝ? በዚህ ዓይነቱ ሰው ጭንቅላት ውስጥ ያለው ተዝለግላጊ ፈሳሽ በእውነቱ አንጎል ይሆን ወይንስ ሌላ? የጠላትን አጀንዳ እንዳለ አንከርፍፎ አንድም ለውጥ ሳያሳዩ ለግማሽ ምዕተ ዓመት መጓዝ፣ በምናባዊ ጦርነት ሕዝብን ማሸበር - ማሸበር የሚለውን ማስበርገግ በሚለው ልተካው መሰለኝ - አዎ - ለዘመናት ሕዝብን ማደናገጥ ምን ይባላል? ዳቦ የምናገኝበትን ምቹ ሁነታ መፍጠር ይቀድማል ወይንስ ቅርጹን እንኳን በወረቅትም ይሁን በጎሊና ለመሳል የሚያስቸግር ግዛት እየፈጠሩ በአዲስ ብሔራዊ ማንነት ዐዋጅ ተዋህዶ የሚኖርን ሕዝብ ግራ ማጋባት? ለዚህ ነው ኦነግ በስም እንጂ በግብር ሊኖር ያልቻለው፡፡ ለዚህ ነው የኦነግ የትግል ሥልትም ሆነ የፖለቲካ አጀንዳ ወንዝ ቀርቶ ምንጭና የደረቀ ኩሬ ሊሻገር ያልቻለው፡፡ ከኦሮሞዎች ጋር አብረን እንኖራለና! እንተዋወቃለና! ግን የአንዳንድ መጤ አስተሳሰቦች ምርኮኞች ደግሞ ምን እንደሚያስቡና ቢሳካላቸው ምን ሊያደርጉ እንደሚችሉም ከአንዳንድ ወሰድ መለስ የሚያደርጋቸው የወቅት ንፋሶች በመነሳት እንገምታለን፡፡ ለዚህም ይመስላል አንዳንድ ወገኖች ከኦነግ ይልቅ ወያኔ እንደሚሻል ከፍርሀታቸው የተነሳ ሲናገሩ የሚስተዋሉት -  ነገሩ ግን ያው ከጅንጀሮ ቆንጆ ዓይነት ነው፡፡ የፈጣሪን እንጠብቅ ሁሉም የሥራውን ያገኛል፡፡ እግዚአብሔር አይተኛም፤አያንቀላፋምም፡፡ ...

ለማንኛውም ከአሁን በኋላ ቀመሩ ሁሉ ይለወጣል፡፡ በዱሮ በሬ ማረስም ይቀራል፡፡ ሕዝቡ የፈረንጅኛውን ፈሊጣዊ ብሂል ተውሶ “Let’s wait until the cat jumps.” ብሎ ሁሉንም እርግፍ አድርጎ ለጊዜ ፍርድ ስጥቶ እንጂ እንደምንገምተው በፍርሀት ተሸንፎ አይደለም፡፡ የ1997ን የቅንጅት መንፈስ ማስታወስ ተገቢ ነው፡፡ ሕዝቡ ፈጣሪ የሚልክለትን በጫትና በሀሺሽ በድራቢውም ማሰቢያ አንጎሉን በሚደፍን በጮማና በዊስኪ ሳይሆን በመንፈስ ቅዱስ የሚመራ ሀገር ወዳድ መሪ ሲልክለት የምናየው ይሆናል፡፡ ካለመሪ ደግሞ ሕዝብ ማለት የንብ ቀፎ ማለት ነው - ንግሥት የሌለው የንብ ቀፎ፡፡ ይደነጋገራል፤ በዝምታም ተውጦ ዙሪያ ገባውን ያዳምጣል፡፡ አለመታደል ሆኖ እንጂ ተቃዋሚዎች በተለይም አነግ ከዚያ አንገብጋቢውን የኢትዮጵያውያን ፍላጎት አመላካች የሚያዚያ 30/97 የሚሊዮኖች ሰላማዊ ሠልፍ ቢረዱ ወልጋዳና ሸፋፋ አቋማቸውን ሊያስተካክሉ በቻሉ ነበር፡፡ ሕዝቡ ጠላት ወዳጁን፣ ጎጂ ጠቃሚውን አጣርቶ አውቋል - ዕድሜ ላለፉት 21 ዓመታት የወያኔ ከፋፋይና ጎጠኛ አገዛዝ፡፡ ኢትዮጵያ የአጭበርባሪዎች መናኸሪያ መሆኗ የሚያበቃበት ዘመን እየመጣ ነው፡፡ ሴተኛ አዳሪዋ አጭበርባሪ አይተኛኝም ያለችው ለካንስ እንደኛው አንጀቷ ቢያርር ኖሯል! አንጀታችንን እኮ አሳረሩት፤ በዚህ ሲሏቸው ‹የዚህ ብሔረሰብ ንቅናቄ› በዚያ ሲሏቸው ‹የዚህ ብሔር ጥምር ግንባር› እያሉ የምንሰማው መልካም ዜና እንዳይኖር አደረጉን፡፡ አፄ ቴዎድሮስ ካህናቱን ‹አንድሽ አንባቢ አንድሽ ተርጓሚ…› በማለት የካህናቱን መሠሪነት ገልጠዋል አሉ፡፡ መሠሪነት አሁንም ተባብሶ ቀጠለና ይሄውና ውሻ በቀደደው ጅብ እየገባ ሀገራችንን መቅኖ አሳጥተዋት ሊቀሩ ነው፡፡ ግን ዕድሜ ለአንድዬ … እንዲህ እንደሆንን አንቀርም … ስሟ እንደገና በዓለም ይገንናል፡፡መቶ ሃምሳው ባንዲራ ጠፍቶ ቀይ ቢጫ አረንጓዴ የወል ባንዲራችን - እጅግ በርካታ የዓለም ሀገራት በምሳሌነቷ ወስደው የቀለማቱን አቀማመጥ እያገለባበጡ የኮረጇት ይህች ባንዴራ ወድቃ አትቀርም፤ ትነሳለች፡፡ የማናውቃቸው ሥውር ኃይላት ይህን የቤት ሥራ እየሠሩ እንደሆነ ይሰማኛል፡፡ እንዳትኮነኑ - የትኛውንም የፖለቲካ ስብስብ ወይም ጉባኤ በአእምሮየ አላሰብኩም፡፡ እንዲሁ ግን የመከራ ደብዳቤያችን እየተቀደደ እንደሆነ በስሜት ደረጃ ሸው የሚለኝ ነገር አለ - አለወትሮየ፡፡- ቢሆንም የኛን ድርሻ ከመወጣት የሚያዘናጋ ነገር እንደሌለ ልጠቁም እፈልጋለሁ፡፡ አቤት ይህን ወረቀትስ የሚያወጣልኝ ድረ ገጽ በጭራሽ አይኖርም እናንተዬ፡፡ እንኳን ከኔ ወጣ እንጂ ምን ተዳዬ? … ግን መናገር ከመጀመሬ ስድስተኛው ገጽ ልግባ? - ፈርዳን ኢንጌሣ መሌ ኢወራኑ - (ፈረስ ያደርሳል እንጂ አይዋጋም)፡፡

አሁንም ለማንኛወም ዘለፋም ሆነ አቃቂር፡- yinegal3@gmail.com